11 ኛ ዓመት ቁጥር 4

ባህርዳር የካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 21July,2006

በኢዩጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

**Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

በአማራ ብሔራዊ ክልሉዊ ምንግስት ምክር ቤት ጠባቂጀነት
የወጣ

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 3-15

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር 122/**1998** ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዓ.ም የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች ማሰፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 12 0/1998 ዓ.ም
የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
አስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

Content

Proclamation No. 120/2006
The Revised Amhara National Regional State Executive Organs, Re

# አዋጅ ቁጥር 122/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና
አጀንሴ አነስተኛ ንግድ ኢንዱስትሪ ስራዎች
ማስፋፊያ ኤጀንሴ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ

በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ጥቃቅንና አነስተኛ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ይበልጥ ማጠናከሩ በከተሞች ስራ አጥነትን ችግር ለማቃለል  አስሶ አደር ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እረገድ ከፍተኛ ማህበራዊና   ንዲኖረውም  ሆነ ተፈላጊውን የሸቀጥ ምርትበማቅረብ ረገድ ከፍተኛ

ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜጣታ እንዳለው በመታመኑ፤

እነዚሁ ድርጅቶች ለመከከለኛና ለከፍተኛ የንግድና ኢንዲስትሪ ተቋማት መሰረቶች በመሆን እንዲጫወቱና ምቹ ሁኔታወችን እንዲፈጠሩ ለማስቻል አስፈላጊውን እጋዛ የሚያደርግና ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚሰጥ ራሱን የቻለ መንግስታዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ  ክልላዊ ም/ቤት በተሸሻለው የክልሉ ህገ -መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ  ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዊች ማስፋፊያ

ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቀጥር 1222/1998 ዓ.ም "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡



**2.**ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. ጥቃቅን የንግድ ሥራ ማለት የተከፈለ ካቲታል 20,000 ያልበለጠ የንግድ ሥራ ማለት ሲሆን ከፍተኛ የቴክኒክኖለጅና የምክር አገልግሎት ተቋማትን አይጨምም፡፡
2. አነስተኛ ንግድ ሥራ ማለት የተከፈለ ካፒታል ከብር 20,000 (ሀያ ሺህ ብር) በላይ የሆነና ከብር 50,000(አምሳ ሺህ ብር) ያልበለጠ የንግድ ሥራ ማለት ሲሆን ከፍተኛ የቴክኖሎጅና የምክር አገልግሎት ተቋማትን አይጨምርም፡፡

ክፍል ሁለት

ስለጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች

ማስፋፊያ ኤጀንሴ መቋቋም፣ ተጠሪነቱ፣ዓላማ ድርጅታዊ አቋምና ስልጣን

**3.** ስለኤጀንሲው መቋቋምና ተጠሪነቱ

**1.** የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች ማስፋፊያ ኤጀንሲ/ ከዚህ በኋላ “ ኤጀንሲው” እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።



**2.** ኤጀንሴው ተጠሪነቱ ለክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ይሆናል።(በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ተሽሯል)

4. ዋና መስሪያ ቤት

1. የለኤጀንሴው ዋና መ/ቤት በባህር ዳር ከተማ የሆናል።
2. የለኤጀንሴው እንደአሰፈላጊነቱ በዞንና በወረዳ ቅርንጫፍና ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

**5.**ዓላማ

ኤጀንሴው የተቋቋመበትን ዓላማ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ሥራዎች እንዲያድጉ፣ እንዲስፋፉና በክልሉ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ አስፈላጊውን

እገዛና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ማስተባበርና ማበረታታት ነው።



6.ድርጅታዊ አቋም

ኤጀንሲው የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር የሚሾሙ ስራ አስኪያጅና ምክትል ስራ አስኪያጅ።

2. በየደረጃው የሚያስፈልጉ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች።

7. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥላጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የአገሪቱን የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ስራዎችን ለማስፋፋትና ለማልማት የሚያስፈልጉ ተስማሚ ቴክኖለጅዎችንና የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ያዘጋጃል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፣ የቴክኒክ፣ ምክርና ሌሎች

አገልግሎቶችን የሰጣል፤

2. የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ሥራዎች የሚሰማሩ ሰወችን ይመዘግባል፣ፈቃድ የሰጣል፣ሥራዎችን ይከታተላል፣ ተገቢውን የስልጠና ዕድል የሚያገኙበትን



7. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኢጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥላጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

3. የአገሪቱን የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ስራዎችን ለማስፋፋትና ለማልማት የሚያስፈልጉ ተስማሚ ቴክኖለጅዎችንና የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ያዘጋጃል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፣ የቴክኒክ፣ ምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን የሰጣል፤

4. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ሥራዎች የሚሰማሩ ሰዎችን ይመዘግባል፣ፈቃድ የሰጣል፣ሥራዎችን ይከታተላል፣ ተገቢውን የስልጠና ዕድል የሚያገኙበትን ሁኔታ ያቻቻል፤

3. በክልሉ ውስጥ የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ስራ ውጤቶች ይታወቁ ዘንድ በየጊዜው ኢግዚቪሽን ያዘጋጃል፣ ሌሎች በሚያዘጋጁቸው ተመሣሣይ ኢግዚቪሽን ይሣተፋል፤

4. ስለክልሉ የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ስራዎች

መረጃዎችን ያሳስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፤

5. የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ማህበራት እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ይደግፋል፣ እድገታቸውን ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ የስልጠና ፍጐቶችን ያጠናል፣ የሙያ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

6. በክልሉ ውስጥ የሙያ ማሻሻያ፣ ቴክኒክና የሰርቶ ማሣያ ማዕከላትን ያቋቁማል።

7. የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ስራዎች በክልሉ ስለሚያድጉበትና ስለሚስፋፋበት ሁኔታ ከፌዴራሉ መንግስትና ከክልል መስተዳደሩ እንዲሁም ከሌሎች አካላትና ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚጋር የተቀናጀ የስራ ግንኑነት ይፈጥራል፤

8.የማመቻቸትና የገቢያ ቦታዎችን እንዲሁም
የብድር አገልግሎቶችን ለማስገኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆ ያመቻቻል፣ ስለብድሩ አመላለስም ክትትል ያደርጋል፤

9. በመስኩ የገቢያና የንግድ ስራ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ለሚመለከተውም ያስተላልፋል፤

10.የጥቃቅንና አነነስተኛ ንግድ ስራ ድርጅቶች እንዲሁም በባለ ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች ነጋዴዎች መከካል የእርስ በርስ ግንኙነትና የመረጃ ልውውጥና ቁርኝት የማድረግ አስፈላጊነቱን ያስተዋውቃል፤

11. በህግ መሰረት ውሎች ይዋዋላል፣ ስምምነቶችን የደርጋል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ የንብረት ባለቤትነት ይሆናል።

**8.**የስራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የኤጀንሲው ስራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7

ስር ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኤጀንሲው ስራዎችበበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

2. የኤጀንሲውን ሥራተኞች በክልሉ ሰቪል ሰርቪስ ሕግ መሰረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ ያሣድጋል፣ ያሰናብታል፤

3. ኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል

4. ለሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

5. የኤጀንሲውን የየሩብ ዓመት፣ ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

6. የኤጀንሲውን የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጠንና ተግባሩን በከፊል ኤጀንሲውን የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**9.**ስለ ምክትል ሥራ አስኪያጁ

የኤጀንሲውን ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጁ ሆኖ፡-

1. በሥራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
2. ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል፡፡

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**10.** ስለበጀት

1. በሌሎች ምንጮች መደገፉ እንደተጠቀ ሆኖ የኤጀንሲው በጀት በክልሉ መንግስት ይመደባል፡፡

**11.**የሂሣብ መዛግብት

1. ኤጀንሲው በተሟሉና ትክክለኛ የሆ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡
2. ኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ፡፡

**12.**የተሸሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

1. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ልማት ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 90/1995 ዓ.ም ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**13.** መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

አዋጅ ቁጥር 90/1995 ዓ.ም ተቋቁሞ የነበረው የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንደዱስትሪ ልማት ቢሮ የጥቃቅንና አነስተ ንግድና ኢንደዱስትሪ ስራዎን በማበረታታት፣ በመደገፍ፣ በማስተዋወቅና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሰረት ወደ ተቋቋመው ኤጀንሲ ተላልፈዋል፡፡

**14.** መመሪያን የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ ንግድና ኢዱስትሪ ቢሮ ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**15.** አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ነሐሴ 13 ቀን 1998 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ክልል

ፕሬዚዳንት